#አጋጣሚ_ወይስ ...?

•

ዛሬ በመጻሕፍ ዳሰሳ በድርሰታቸው አንቱ የተባሉትን ሁለት ጎምቱ ደራሲዎች የፈጠራ ውጤት የሆኑትን መጻሕፍቶች ለመቃኘት እንሞክራለን።

ክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁና በዓሉ ግርማ በራሳቸው የአግባፍ ዘውግ እውቅናናን ከማትረፍ በላይ እስከ አሁን ድረስ መጻሕፍቶቻቸው ጣዕማቸ እየጨመረ በትውልድ ትውልድ ተነባቢነታቸው ቀጥሏል። ፍቅር እስከ መቃብር በ 1958 ዓ/ም ታትሞ ለንባብ በቅቷል። ሀዲስ ደግሞ የመጀመሪያ ዕትሙ 1975 ዓ/ም ነው። ከስራዎቻቸው መካከል ፍቅር እስከ መቃብርና ሀዲስን ምን አገናኛቸው፣ አመሳሰላቸው? በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን።

የፍቅር እስከ መቃብር ዋና ጭብጥ (Theme) በወቅቱ የነበረውን የፊውዳል ስርዓት ግዜ ከማይሽረው ፍቅር ጋር እያዋዛ መገሰፅ፣ መኮነን፣ ማውገዝ ነበር። የጭሰኛና ባላበት ስርዓት የሰው ልጅ በተፈጥሮ የተለገሰውን ነፃ ማንነት የሚነፍግ ነው። ይሄም መሰረታዊ የሰው ልጅ ሰበዓዊ መብት የሚጥስ ነበር። ሰውን በብሄሩ፣ በቀለሙ፣ በሀይማኖቱ ፈጣሪ የለገሰውን እኩል ሰውነት ማጉደፍ ተገቢ ስላልነበረ በወቅቱ ትልቅ የህዝብ ቁጣንና አመፅን ሊቀሰቅስ ችሏል። ይሄም አሁን ላለንበት ለውጥ መሰረቱን እንደጣለ እሙን ነው። የፊውዳሉን ስርዓት በጥቂቱም ቢሆን ለመግለፅ እንደተሞከረው አንድ በሰውነት ለሚያምን ግለሰብ የሚዋጥ አልነበረም። ሀዲስ አለማየሁ በፍቅር እስከ መቃብር ደርሰታቸው ከሁሉም ነገር ሰውነት እንደሚቀድም ከጊዜው ቀድመው ተናግረዋል። በተመሳሳይ ደግሞ በዓሉ ግርማ በ"ሀዲስ" ስራው በዋናነት ለማሳሰብ ሞክሯል።

እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ዕልፍ ባህሎች ባለቤት እንደሆነች ይታወቃል። ግን ጠቃሚ ባህሎች እንዳሉ ሁሉ ጎጂ ባህሎች አሉ። ለምሳሌ በወቅቱ ኢትዮጵያ በነበራት ዘውዳዊ ስርዓት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሚና ቀላል አልነበረም። በመሆኑ በየዕለቱ የሚውሉ የአማልክት ቀኖችን በመሰየም ህዝቡ ስራ እንዳይሰራ ሲደረግ እንደነበር ይነገራል። ሀዲስም በዓሉም የዚህ አጉል ልማድ ተቃዋሚ እንደነበሩ ሁለቱን ድርሰቶቻቸውን ማንበብ በቂ ነው። ልደታ፣ ስላሴ፣ ሚካዔል...እያሉ ስራ መስራትን ማውገዝ ትክክል እንዳልነበረ የሀገራችንን የስልጣኔ ማሽቆልቆል ተገቢ ማሳያ ነው።

ሁለቱም ድርሰቶች መቼት በደራሲዎቹ ትውልድ አከባቢ መከተሙ ያመሳስላቸዋል። የሀዲስ ትውልድ ስፍራ በእንጾር ኪዳነ ምህረት ቢሆንም ለዲማ ቅርብ ናቸው፣ የፍቅር እስከ መቃብር መቼት እዛው ዲማ ጎርጊስ። የበዓሉ ትውልድ ስፍራ ሱጴ፣ የሀዲስ መቼት እዛው ሱጴ መሆናቸው ምናልባት ያጋጣሚ ይሆን?

ሌላው ደግሞ የተመሳሰለብኝ የገፀ ባህርያት አወቃቀር ነው። እስቲ ለማየት እንሞክር:-

የፍቅር እስከ መቃብር ዋና ገፀ ባህሪ በዛብህ ለውድነሽና ለቦጋለ ብቸኛ ልጅ ነው። በተመሳሳይ ደግሞ የሀዲስ ዋና ገፀ ባህሪ ሀዲስ ለእልፍነሽና ለሳህሌ ብቸኛ ልጅም ነበረ።

ሁለቱም ዋና ገፀ ባህርያት በተለያየ ምክንያት ቢሆንም ከትውልድ ስፍራቸው ወደ ሌላ ቦታ አቅንተዋል። በዛብህ ከትውልድ ስፍራው ማንኩሳ ወደ ዋናው መቼት ድማ ጎርጊስ ሲያቀና ሀዲስ ደግሞ ከአ/አ ወደ ሱጴ የታሪኩ ዋና ማጠንጠኛ ከተማ ተጉዟል። ሁለቱም ዋና ገፀ ባህሪያት የሚያስተምሩት ት/ት የተለያየ ቢሆንም መምህሮች ነበሩ።

ሁለቱም ዋና ገፀ ባህሪዎች በፍቅር የወደዷቸው ሴቶች የባላባት ልጆች ነበሩ። ምናልባት ደራሲዎቹ በወቅቱ አይነኬ፣ አይደፈሬ የነበረውን የባላባት ልጅን ለጭሰኛ ልጅ በፍቅር በማጣመር የነበረውን ግንቡን በማፍረስ ሰው ሁሉ እኩል መሆኑን በድፍረት ተናግረዋል። ሰብለ የፊታውራሪ መሸሻ ልጅ ስትሆን አይናለም ደግሞ የፊታውራሪ ተካ ልጅ ናት። ሁለቱም ፊታውራሪዎች የከተማው ባላባት ናቸው። ሁለቱም ፊታውራሪዎች ከቤት የማይጠፉ የነፍስ አባት ቄሶች ነበሯቸው። ሁለቱም ፊታዎራሪዎች የፊውዳሉ ስርዓት ማብቃትን ባለመቀበላቸው አሟሟታቸው በተለያየ መንገድ ቢሆንም በመጨረሻ አርፈዋል። ሰብለና አይናለምም ለወላጆቻቸው ብቸኛ ልጆች ናቸው። ሁለቱም ሴቶች (ሰብለና አይናለም) በተለያየ ምክንያት ቢሆንም የመጀመሪያ ስርጋቸው ሳይሳካ ቀርቷል። ሁለቱም ደግሞ ስርጋቸው ሲሰረግ ፍቅር ውስጥ ነበሩ።

ሌላው ደግሞ በገፀ ባህሪ ሚና የተመሳሰሉትን ልጠቁም:-

•በዛብህ ከሀዲስ ሁለቱም የተረጋጉ፥ አስተዋዮች፥ ብሩህ ጭንቅላት የታደሉ ናቸው፤
•ሰብለ ከአይናለም ሁለቱም ቆንጆ ሆነው ግን ሳያገቡ የቆዩ፥ዝምተኛና አይናፋር ይመስላሉ፤
•ጉዱ ካሳ ከታፈሰ ሁለቱም የሰው ምክር የማይሰሙ፥ በራሳቸው፥ በመሰላቸው ሚዛዙ፥ አይነኬ ስርዓቶችን የጣሱ ናቸው፤
•ፊታውራሪ መሸሻ ከፊታውራሪ ተካ ሁለቱም ባላባት ናቸው፣
•ቄስ ሞገሴ ከመምሬ መሀሪ ከየፊታውራሪ ቤታቸው የማይጠፉ፣ ጠጅ መጠጣት በጣም የሚወዱ፣ ፊታውራሪያቸውን የሚገስፀ። ግን ሁለቱም ገደል ማሚቶ ነበሩ።

ስለዚህ ከላይ በ charcter ሚና ደረጃ የገለፅናቸው ገፀ ባህሪዎች መመሳሰል ይታይባቸዋል።

በመጨረሻ በዓሉ ግርማ የመጻሕፉን ስያሜ እና መሪ ገፀ ባህሪውን "ሀዲስ" በማለት የከቡር ዶ/ር ሀዲስን ስም የወሰደ ይመስላል። ምናልባትም ከላይ የተመለከትናቸውን መመሳሰሎች የተዋሰ ሊሆን ይችላል። ይሄም ካለው መውደድ፣ አድናቆት፣ አክብሮት ነው ሊሆን የሚችለው።

እናም ሁለቱም እስከ አሁን ድረስ ካነበብኳቸው መጻሕፍት ወደር የማይገኝላቸው መሆናቸውን በእርግጠኝነት ለመናገር እወዳለው። በጣም ድንቅ መጻሕፍት ናቸው። ከዚህ በኋላ እነሱን የመሰለ መጻሕፍትም ይፃፋል ብዬ ተስፋ አላደርግም። ስለዚህ ሁለቱም ደራሲዎች በአካል ከእኛ ጋር ባይኖሩም በዕውብ ድንቅ ስራዎቻቸው በመንፈስ ለዘላለም ከእኛ ጋር ይኖራሉ። እኔም ለሁሉቱም ጉምቱ ደራሲዎች ያለኝን መውደድ፣ ክብርና አድናቆት ከወገቤ ዝቅ ብዬ ልገልፅላቸው እወዳለው።

#ቸር_ጊዜ!
•
#በአንተነህ
#እሁድ ግንቦት ፲፰ ቀን ፳፻፲፭